**ጋዜጣዊ መግለጫ**

**“በግጭትም ሆነ በሰላም ወቅት ፆታዊ ጥቃት ይቁም!”**

*አዲስ አበባ፤ ሕዳር 16 ቀን 2015 ዓ.ም.*

የ16ቱ ቀናት ፆታዊ ጥቃትን እናስቁም ንቅናቄ ላለፉት 25 አመታት በሃገር አቀፍ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሴቶችን ጥቃት ለማስቀረት የተደረጉ እንቅስቃሴዎችን የማስተባበሪያ አይነተኛ መንገድ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ኖቬምበር 25 ዓለም አቀፍ የሴቶች ጥቃት መከላከል ቀን፤ የንቅናቄው ማስጀመሪያ እንዲሁም ዲሴምበር 10 የሰብአዊ መብት የንቅናቄው መጠናቀቂያ ቀን ሆነው የተመረጡት የሰብአዊ መብት ዕሴቶች ቁርኝትን አፅንኦት ለመስጠት እና የሴቶች ጥቃት ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ጥሰት መሆኑን ለማመልከት ነው፡፡

ዘንድሮም ይህ ዓለም አቀፍ ዘመቻ በፆታዊ ጥቃት እንቅስቃሴ ከህዳር 16 እስከ ታህሳስ 1 ቀን 2015 ዓ.ም የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ይካሄዱበታል ፡፡ “ዘመቻ በፆታዊ ጥቃት - ኢትዮጵያ” ፆታዊ ጥቃትን በጋራ ለመከላከል የተቋቋመ የሲቪክ ድርጅቶች ቡድን ሲሆን የሴቶች ማህበራትና ፆታዊ ጥቃትን እንደ አጀንዳ አርገው የሚሰሩ ሌሎች ድርጅቶችን ያካተተ በኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት (ኢ.ሴ.ማ.ቅ) የሚመራ ቡድን ነው። ይህ ቡድን የዘንድሮውን የ16ቱን ቀናት ንቅናቄ “በግጭትም ሆነ በሰላም ወቅት ፆታዊ ጥቃት ይቁም! ዝም አንበል!” በሚል መሪ ቃል በይፋ ጀምሯል፡፡

“ዘመቻ በፆታዊ ጥቃት - ኢትዮጵያ” ቡድን በሴቶችና ወጣት ሴቶች ላይ ከቤት እስከ አደባባይ ስለሚፈፀሙ ጥቃቶች አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ ከተሞች የምክክርና የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን ያዘጋጀ ሲሆን ከፆታዊ ጥቃት ጋር በተያያዘ ተጠያቂነትን በተሻለ ደረጃ ለማረጋገጥ ከህግ አንፃር ሊከናወኑ በሚገቡ ተግባራት ላይም ውይይት የሚደረግ ይሆናል። በሴቾች መብቶች ላይ የሚሰሩ አካላትን በማሰባሰብ፣ ልምዶችን በመለዋወጥ የተገኙ ውጤቶችና ያጋጠሙ ችግሮች የሚታዩበት መድረከም ተዘጋጅቷል።

ከግንዛቤ ማስጨበጫና የቅስቀሳ ሥራዎች በተጨማሪ ቡድኑ በግጭት ምክንያት ከቀዬአቸው ለተፈናቀሉ ሴቶችና ህፃናት እንዲሁም አረጋዊያን “ለእህቴ” በሚል የእርዳታ ማሰባሰቢያ መርሃግብር በማካሄድ አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ እንቅስቃሴ ጀምሯል፡፡ ህብረተሰቡም ይህንን ዓላማ ተገንዝቦ ቀና ትብብሩን እንዲያደርግ፣ የግልና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም የበኩላቸውን ሃላፊነት እንዲወጡ ቡድኑ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

ቡድኑ የዚህ አመት መሪ ቃል “በግጭትም ሆነ በሰላም ወቅት ፆታዊ ጥቃት ይቁም! ዝም አንበል!” እንዲሆን የወሰነው በአገሪቱ ከሁለት ዓመታት በላይ በዘለቀው የሰሜን ኢትዮጵያ ግጭት እንዲሁም በሌሎቹ የአገሪቱ ክፍሎች በተቀሰቀሱ ግጭቶች ሴቶችና ህጻናት ግንባር ቀደም ተጎጂዎች በመሆናቸው ጉዳዩ ተገቢው ትኩረት እንዲደረግበትና ሴቶችና ወጣት ሴቶች ከጥቃት ከለላ እንዲያገኙ የሚመለከታቸውን አካላትና መላውን ማኅበረሰብ ለማሳሰብ ነው፡

በሰሜን ኢትዮጵያው ግጭት በርካታ ሴቶች ላይ ጥቃት መፈፀሙ በሰብዓዊ መብት ድርጅቶችና በሌሎችም ተቋማት ሪፖርት መደረጉ ይታወቃል። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሴቶች በተፈፀመባቸው ጥቃት ለአካላዊና ስነልቦአናዊ ጉዳት ተጋልጠዋል። ከግጭት ውጭም በሴቶችና፤ ወጣት ሴቶች ላይ ጭምር ፆታዊ ጥቃት እንዲሁም ግድያ እየተፈፀመ እንደሆነም በየጊዜው የሚወጡ ሪፖርቶች ያመለክታሉ።

የዘንድሮው 16ቱ ቀናት ንቅናቄ እንደ ሁልጊዜውም ፆታን መሰረት ባደረጉ በሴቶች ላይ የሚደርሱ የጥቃት ወንጀሎችን በተለይም በግጭት

እና ከመኖሪያ አካባቢ በመፈናቀል ምክንያት በሚደርሱ ፆታዊ ጥቃቶች ላይ ልዩ ትኩረት ያደርጋል፡፡ በሴቶች ላይ የሚደርሱ የፆታዊ ጥቃት ተግባራት የሴቶችን የህልውና፤ አካል ጥበቃ፤ በስነ-ልቦና እና ኑሮ ባጠቃላይ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግሮችን የሚያስከትሉ ናቸው። ስለዚህም ለዚህ ጉዳይ ሰብዓዊ መብት እይታ ካልታከለበት ሴቶችን ከጥቃት መከላከል የበጎ ስራ አገልግሎት ተደርጎ እንዲወሰድ ያደርጋል። የሴቶች ከፆታዊ ጥቃት መጠበቅ የሰብአዊ መብት ጉዳይ ነው። በሴቶች ላይ ጥቃት ሲፈፀም የሴቶች ሰብዓዊ ክብር በከፍተኛ ሁኔታ የሚጣስ እንደመሆኑ ማንኛውም ሁኔታ ጥቃቱን ሊያቀልና ምክንያት ሊሆን አይገባም። ከዚህ አንፃር በተለያየ ወቅት የምንሰማው ተጎጅዎችን ድጋሚ ተጎጂ (Double victimization) ከሚያደርጉ አባባሎች አስተሳሰባችንን ልንታገል ይገባል። ግጭት በሴቶች ላይ ለሚደርስ መደፈር ምክንያት ሊሆን አይገባም። ሴቶችና ህፃናት በስራ ቦታ፣ በትምህርት ቤት፣ በቤተሰብ ፣በተለያዩ ቦታዎች፣ በጦርነት ውስጥ በመደፈራቸው ከምን ግዜውም በላይ መንግስት ተጠያቂነትን በማስፈን፣ ሲቪል ማህበራትና ህብረተሰብ አነቃቂዎች ግንዛቤ በመፍጠርና በጉዳዩ ላይ ማህበረሰባዊ የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት መስራት ይኖርባቸዋል።

በዚህም መሰረት ዘመቻ በፆታዊ ጥቃት ኢትዮጵያ ሴቶችና ህፃናት ከጥቃት እንዲጠበቁ ሁሉም የበኩልን ሃላፊነት ይወጣ ዘንድ ለመንግስት ፣ ለህብረተሰቡና መንግሥታዊ ላልሆኑ ተቋማት ጥሪውን ያስተላልፋል። ህብረተሰቡ ከቤት እስከ አደባባይ የሴቶችን ጥቃት መከላከልና መቃወም ይኖርበታል፤ መንግሥትም በግጭትም ሆነ በሌሎች ሁኔታዎች ውስጥ በሴቶች ላይ ለሚፈፀሙ ፆታዊ ጥቃቶች የህግ ተጠያቂነት መስፈንን ማረጋገጥ ይገባዋል። ፆታዊ ጥቃት የተፈፀመባቸው ሴቶች አስፈላጊውን የህክምና፣ የህግና የስነልቦና ድጋፍ እንዲያገኙ መንግሥታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲተባበሩም ዘመቻ በፆታዊ ጥቃት ኢትዮጵያ ጥሪውን ያስተላልፋል። ፆታዊ ጥቃት ሰብዓዊ መብት ጥሰት ስለመሆኑም ማህበረሰቡን፣ ህግ አስከባሪዎችን ጨምሮ የተለያዩ የመንግስት አካላትን ግንዛቤ በማስጨበጥ እንቅስቃሴያቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ በሴቶች መብቶች ላይ የሚሰሩና ሌሎች ሲቪክ ማህበራትን ቡድኑ ያሳስባል።

**ለተጨማሪ መረጃ፡**

በስልክቁጥር +251-118-217758/57 ወይም በኢሜል newaethiopia@gmail.com ይጠይቁ፡፡